# የፌዴራል የሰበርና የሰበር ሰበር የስልጣን ምንጭ ገልጠን ብናየው! (በሰበር መ.ቁ. 26996 እና 31601 መነሻነት የቀረበ ትችት)

መሓሪ ረዳኢ*

## 1. መግቢያ

ኢትዮጵያ ከ1980ዎቹ አጋማሽ ወዲህ ከአሃዳዊ (unitary) መንግስታዊ ስርአት ወጥታ በፌዴራላዊ መንግስታዊ መዋቅር እየተዳደረች መሆንዋ የሚታወቅ ነው፡፡ በፌዴራሉ አወቃቀር መሰረት ዋነኞቹ መንግስታዊ ስራዎች ማለትም የህግ አውጪነት፣ የህግ አስፈጻሚነትና የህግ ተርጓሚነት ተግባራት በፌዴራል መንግስት ደረጃና በፌዴራል መንግስቱ አባላት (ክልሎች) ደረጃ እንደሚከናወኑ በፌዴራሉ ህገ-መንግስት ተመልክቶ ይገኛል፡፡[1] በመሆኑም በፌዴራል ደረጃ የህግ አውጪነት ስራ የሚያከናውን የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት፤ የህግ አስፈጻሚነቱን ተግባር የሚመራና የሚያስተባብር በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራ የሚኒስትሮች ም/ቤት፣ እንዲሁም የህግ ተርጓሚነቱን ስራ የሚሰራ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሚመራ ሶስት እርከኖች ያሉት የዳኝነት ስርአት ተዋቅሮ ይገኛል፡፡ በአባል የክልል መንግስታት ደረጃም በተመሳሳይ ሁኔታ የህግ አውጪነቱ ሃላፊነት በክልል ምክር ቤቶች፣ የህግ አስፈጻሚነቱ ስራም በክልል ርእሰ መስተዳድር በሚመራ ካቢኔ፣ እንዲሁም የዳኝነት ተግባራቱን በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ስር በተደራጁ ፍ/ቤቶች በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡

ህገ-መንግስቱ ተቋሞቹን በማደራጀት ላይ ሳይወሰን የስልጣን ክልላቸውንም ጭምር በህግ ለይቶ ለማስቀመጥ ጥረት አድርጓል፡፡ ለዚህ ይረዳ ዘንድም የፌዴራል መንግስቱን ስልጣን ለይቶ በማስቀመጥ ከዚያም በመቀጠል የፌዴራል መንግስቱንና የክልል መንግስታትን የጋራ ስልጣን የሆኑትን የዘረዘረ ሲሆን ከዚህ ውጭ ያለ መንግስታዊ ስልጣን ግን የየክልሉ ስልጣን እንደሆነ በማያሻማ መንገድ አስቀምጦ ይገኛል፡፡[2] ነገር ግን ህገ-መንግስቱ የሚጠቀምባቸው ቃላት ጠቅለል ያሉና በመሰረታዊ መርሆዎች ደረጃ የሚመደቡ በመሆናቸው በወረቀት ላይ ግልጽና የማያሻሙ መስለው የሚታዩትን ያህል በእለት ተእለት የስራ አፈጻጸምና ክንውን ላይ ግን የዚያኑ ያህል ጠርተው አይታዩም፡፡

በዚህ አጭር ጽሁፍ ውስጥ ከሶስቱ መንግስታዊ አካላት በአንዱ ማለትም በዳኝነት አካሉ ላይ በተለይም በሰበር ችሎቱ ላይ ብቻ በማትኮር ህገ-መንግስቱ የፌዴራልና የክልል የዳኝነት አካላት በሰበር ክንውን ዙሪያ እንዴት እንዳደራጃቸውና በተጨባጭም እንዴት እየሰሩ እንደሆነ ለመመርመር እንሞክራለን፡፡ የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በክልል ሰበር ሰሚ ችሎቶች የታዩትን የክልል ጉዳዮች በድጋሚ እያስቀረበና እየመረመረ ያለው በዚህ ረገድ በህግ የተሰጠ ስልጣን ሳይኖረው ነው ብሎ ይከራከራል፡፡

---

*ረዳት ፕሮፌሰር፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ሕግ ት/ቤት (LLB.;LL.M;Ph.D.Candidate)፣E-mail: me2ha1@yahoo.com.

[1] የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት አንቀፅ 50(2)

[2] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 52(1)

ሰበር ሰሚ ችሎቱ ከስልጣኑ ውጪ የሆኑትን ጉዳዮች እያስቀረበ በመመርመር ላይ በመጠመዱ ከአቅሙ በላይ የሆነ የጉዳይና የባለጉዳይ መጠን ተከማችቶበት ለያንዳንዱ ጉዳይ መመደብ ያለበት ጊዜና የሰው ሃይል እያነሰ ውሳኔዎችን በወቅቱና በጥራት ለመስጠት እየተቸገረ እንደሆነ ይታያል። ስለሆነም የባለጉዳዮችን ጊዜና ውጪ እያናረ፣ እንዲሁም የራሱን ውሱን ጊዜ፣ አቅምና ሃብት በህገ-መንግስቱና በህግ አውጪው ላልተመደበ ጉዳይ እያባከነው ይገኛል የሚለው የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ እምነት ነው። እንዲያውም በዚሁ አካሄድ ከተቀጠለ የፌዴራሉ ምሰሶዎች ከሆኑት አንዱ የሆነውንና በህገ-መንግስቱ እውቅና ያገኘውን በዳኝነት ረገድ ክልሎች ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩበት ስርአት እንዳይሸራረፍ ብሎም እንዳይናድ ስጋት አለው። ለዚህም የክርክር ጭብጡን በቀጣዮቹ የጽሁፉ ክፍል ያቀርባል። ይህ ፀሐፊ ያቀረበው አጭር ፅሁፍ በጉዳዮ ላይ የሰከነና ቀጣይነት ያለው የሃሳብ ልውውጥ እንዲካሄድ በር ይከፍታል ብሎ ያምናል።

## 2. የሃገሪቱ የዳኝነት ስርአት ህገ-መንግስታዊ ማእቀፍ

በፌዴራል ህገ-መንግስቱ ውስጥ የዳኝነት ነጻነት ስልጣንና አወቃቀርን የሚደነግግ ራሱን የቻለ ምእራፍ የተመደበ ሲሆን በስሩም ብዛት ያላቸው ንኡሳን አንቀጾች ያካተቱ አራት አንቀጾች ይገኛሉ።[3] በእነዚሁም መሰረት ከህግ በቀር በሌላ አካል የማይመሩ ነጻ የዳኝነት አካላት በፌዴራልም ሆነ በክልል ደረጃ መመስረታቸው የተበሰረ ሲሆን እያንዳንዳቸው ሶስት ደረጃዎች ያሉዋቸው የፍርድ ቤት መዋቅሮች እንደሚደራጁም ተመልክቷል።

በርግጥ የዳኝነት መዋቅሩም እንደ ህግ አውጪውና እንደ ህግ አስፈጻሚው በፌዴራልና በክልል ደረጃ የየራሱ መስመር ይዞ በትይዩ (parallel) መልክ የተደራጀ ነው።ነገር ግን በተግባር ደረጃ የፌዴራልና የክልል የዳኝነት አካላት የሚያገናኛቸው በርካታ ጉዳይ እንዳለ ይታወቃል። እንዲያውም በክልል ውስጥ ለሚከናወኑ የፌዴራል የዳኝነት ጉዳዮች በመርህ ደረጃ የክልል ፍርድ ቤቶች በህገ-መንግስት በተሰጣቸው ውክልና መሰረት የሚያከናውኑት ተግባር ነው። ስለሆነም የፌዴራል የዳኝነት አካሉ የራሱ የፍርድ ቤት መዋቅር ባላቋቋመበት ክልል ውስጥ የየክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤቶችት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን በመወከል፤ የየክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤቶች ደግሞ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ተክተው ጉዳዮችን ማስተናገድ እንዳለባቸው በህገ-መንግስቱ ሰፍሮ ይገኛል።[4]

ከዚህ በተጨማሪም ምንም እንኳ በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ስልጣን እንዲሁም የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ደግሞ በክልል ጉዳዮች የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ስልጣን የተሰጠው ቢሆንም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግን መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበትን የፌዴራልም ሆነ የክልል ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ ውሳኔ በሰበር ለማየት ስልጣንና ሃላፊነት ተሰጥቶታል።[5] በመሆኑም የፌዴራልና የክልል የዳኝነት ስርአቱ ብዙ መገናኛ ነጥቦች ያሉት ነው።

---

[3] ዝኒ ከማሁ ምእራፍ ዘጠኝ (ከአንቀጽ 78-81)

[4] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 80(2) እና (4)

[5] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 80(3)(ሀ)

ለዚህም የተሰጠው ምክንያት በሃገር ደረጃ ወጥነትና ተገማችነት ያለው የህግ አተረጓጎም ስርአት ለማዳበር ካለ ፍላጎት የመነጨ ስለመሆኑ ህገ-መንግስቱ ሲረቀቅ ከተደራጁ ቃለ-ጉባኤዎች መገንዘብ ይቻላል።[6] በፌዴራልና በክልል ህግ አውጪና ህግ አስፈጻሚ አካላት መካከል ግን እንዲህ ዓይነት የተደበላለቀ የስራ ግንኙነት አይታይም።

ይህ አይነቱ የዳኝነት አካላት አሰራር ከፌዴራላዊ ስርአት የስልጣን ክፍፍል አንጻር እየታየ የሚደገፍበትና የሚነቀፍበት ምክንያት የሚቀርብ ቢሆንም በዚህ ጽሁፍ ትኩረት የተደረገበት ነጥብ ግን ከዚህ ወጣ ያለ ነው። በዚህ ጽሁፍ ለመዳሰስ የተፈለገው ነጥብ ህገ-መንግስቱ የወሰደው አቋም የሚነቀፍበትም የሚወደስበትም ምክንያት እንዳለ ሆኖ፤ ለመሆኑ እየተሰራ ያለውስ በህገ-መንግስቱ መሰረት ነው ወይ? የሚለው ነው። ጉዳዩን በተጨባጭ ለማብራራት እንዲያመቸንም የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መርምሮ ውሳኔ የሰጠባቸውን ሁለት መዝገቦች በምሳሌነት ወስደን እናያለን።

## 3. የጉዳዮቹ አጭር ዘገባ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ከሰጠባቸው ጉዳዮች ውስጥ ለዚህ ውይይት የተመረጠው አንዱ ጉዳይ የሰበር መዝገብ ቁ. 26996 ነው። ወደ ዋናው ጉዳይ ከመግባታችን በፊት ግን አንድ ነጥብ ማስገንዘብ ይገባል። ይኸውም የዚህ ጽሁፍ ዋነኛ ትኩረት ሰበር ሰሚው ችሎት ጉዳዩን ያየው በስልጣኑ ክልል ስለመሆኑ ወይም አለመሆኑ ለመመርመር በመሆኑ ሰበር ችሎቱ በክርክሩ ዋና ይዘት (substance) ላይ የሰጠውን ውሳኔ በተመለከተ በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የሚሰጥ ትችት አይኖርም። የጽሁፉ አላማ በስነ-ስርአታዊ (procedural) ጉዳዮች ላይ የተገደበ ነውና።

ወደ ጉዳዩ ስንገባ በዚህ መዝገብ የተያዘው ነጥብ በሽያጭ ውል ላይ የተነሳን ክርክር ለመፍታት የቀረበ ክስ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የጅማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፊት ነበር። የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባለጉዳዮችን አከራክሮ ውሳኔ የሰጠበት ሲሆን በውሳኔው ቅር የተሰኘው ወገንም ይግባኙን ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አስቀርቦ አሰምቷል። የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤቱም የስር ፍርድ ቤቱን ውሳኔ ሽሮ የራሱ ጭብጥ መዝዞ በማውጣት የስር ፍርድ ቤቱ ውሳኔ እንዲሰጥበት መዝገቡን በፍ/ብ//ሥ/ሥ/ ህግ ቁጥር 343 መሰረት ለስር ፍርድ ቤት መልሶታል። በጠቅላይ ፍ/ቤቱ ውሳኔ ቅር የተሰኘው ወገን ግን ወደ ስር ፍ/ቤት ወርዶ ከመከራከር ይልቅ ውሳኔው መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በሚል ጉዳዩን ወደ ክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አቀረበው። ነገር ግን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር አቤቱታውን ውድቅ አደረገው። አመልካቹ በመጨረሻ የወሰደው አማራጭ ጉዳዩን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በማቅረብ 'የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝና በሰበር ደረጃ የወሰደው አቋም መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው' በሚል ጉዳዩ በሰበር እንዲታይለት አቤቱታ ማቅረብ ሆነ። የፌዴራሉ ሰበር ችሎትም አቤቱታውን ተቀብሎና አከራክሮ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝና በሰበር የሰጠውን ውሳኔ በመሻር የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማጽናት ጉዳዩን ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እልባት ሰጥቶታል።

[6] Muradu Abdo, *infra note 10*, at 69.

ከዚህ ጋር በተመሳሰለ መንገድ በሰበር መዝገብ ቁ. 31601 ስር በአዲስ አበባ ከተማ ከቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት ተነስቶ በይግባኝ ወደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የቀረበን ጉዳይ በመጨረሻም በከተማው አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ታይቶ መጨረሻነቱ ያበቃለትን የቤት ኪራይ ክርክር የፌዴራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር ሰሚነት ስልጣኑ አስቀርቦ በመመርመር ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡ በመጨረሻም የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤትን ውሳኔ አጽንቷል፡፡

እነዚህ ሁለት ጉዳዮች አንዳንድ ተመሳሳይነት ይታይባቸዋል፡፡ ሁለቱም ተራ የውል አለመፈጸም ክርክር ሲሆኑ፣ የውል ጉዳዮች ደግሞ በክልል ጉዳዮች ስልጣን ስር የሚያርፉ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በየአስተዳደራቸውም ባሉ የዳኝነት አካላት ታይተውም የመጨረሻ ውሳኔ አግኝተዋል፡፡ እንዲያውም የኦሮሚያው ጉዳይ ከመጨረሻ ውሳኔነት አልፎ በክልሉ ሰበር ችሎትም ታይቷል፡፡ ከእነዚሁ የመጨረሻ ውሳኔዎች በኃላም የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የመጨረሻ ውሳኔ ባረፈባቸው የህግ ጉዳዮች ላይ የሰበር ስልጣን አለኝ በሚል እምነት አስቀርቦ በመመርመር ውሳኔ ሰጥቶባቸዋል፡፡ በሁለቱም ጉዳዮች የስር የዳኝነት አካላት ውሳኔዎች በፌዴራል ሰበር ችሎቱ ፀንተዋል፡፡

በሌላ በኩል ግን በሁለቱ ጉዳዮች መካከል ትኩረት የሚሹ ልዩነቶች ይታያሉ፡፡ አንደኛ የኦሮሚያው ጉዳይ የተነሳው ከመደበኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአዲስ አበባው ግን ከቀበሌ ማህበራዊ ፍ/ቤት የተነሳ ነበር፡፡ ሁለተኛ የኦሮሚያው ጉዳይ በክልሉ ውስጥ በክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ጭምር ታይቶ ያበቃለት ሲሆን የአዲስ አበባው ግን በከተማው አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በይግባኝ ደረጃ መመርመሩን እንጂ በከተማ አስተዳደሩ በሰበር ስለመታየቱ መዝገቡ አያመለክትም፡፡ በከተማ አስተዳደሩ ውስጥ የሰበር ችሎት ስለመኖሩም የተመለከተ ነገር የለም፡፡ ሶስተኛ ኦሮሚያ በህገ-መንግስቱ ውስጥ በክልል መንግስትነት ታውቆ የተመዘገበ ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ግን የተሟላ የክልል መንግስትነት ስልጣን አለው ለማለት የሚያስደፍር አይደለም፡፡ እንዲያውም ተጠሪነቱ ለፌዴራሉ መንግስት ስለመሆኑ በህገ መንግስቱ በግልጽ የተመለከተ ሲሆን[7] ከፌዴራል መንግስቱም በተለይ ለፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ተጠሪ መሆኑ ማቋቋሚያ አዋጁ ይደነግጋል፡፡[8]

## 4. ለሰበርና ለሰበር ሰበር መሰረት የሆነው የህገ-መንግስት ድንጋጌ ይዘት

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የስልጣኑ መሰረት አድርጎ የሚጠቀምበት የህገ መንግስቱ ድንጋጌ በፌዴራል ህገ-መንግስቱ አንቀጽ 80 ሥር የተመለከቱት ንኡሳን አንቀጾች ሲሆኑ ከተያዘው ጉዳይ ጋር አግባብነት ያላቸው እንደሚከተለው ይነበባሉ፡፡

> *1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል፡፡*
>
> *2. የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በክልሉ ጉዳይ ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል፡፡...*

---

[7] የኢፌዲሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 49(3)

[8] የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ፡ ቁ.361/1995 አንቀጽ 61(5)

*3. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 እና 2 የተጠቀሰው ቢኖርም*

*ሀ) የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበትን ማናቸውም የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ስልጣን ይኖረዋል። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል (ሰረዝ የተጨመረ)።*

*ለ) የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበትን በክልል ጉዳዮች የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ስልጣን ይኖረዋል። ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል ይላል።*

## 5. ትንተና

እንግዲህ ከዚህ በላይ ለማሳየት እንደተሞከረው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት 'በህገ-መንግስቱ የተሰጠኝ ስልጣን ነው' በሚል እምነት በክልልም ሆነ በከተማ አስተዳደር የዳኝነት አካላት በተሰጡ የዳኝነት ውሳኔዎች ላይ 'የሰበር ስልጣኑን' በመጠቀም በክልል ደረጃ በሰበር የታዩትንም ጭምር እየመረመረና ውሳኔ እያሳረፈ ይገኛል። የማህበረሰባችን አልረታም ባይነትና በንጉሱ ዘመን የነበረው 'የዙፋን ችሎት' የቀረጸው የአዲስ አበባ የፍትህ የመጨረሻ ምንጭነት የታሪክ ግጥጥሞሽ ሆኖ በክልል ደረጃ ያበቃላቸው ጉዳዮች በሰበር ሰበር ለማሳየትና 'የመጨረሻ እድል ለመሞከር' እጅግ በርካታ ጉዳዮች ከየክልሉ ወደዚሁ ችሎት እየጎረፉ ናቸው። እንዲህ አይነቱ ሁኔታም ፌዴራላዊ መዋቅሩን ወደ አሃዳዊ ስርአት እንዳይመልሰው ከመስጋት በተጨማሪ የባለጉዳዮችን ጊዜና ወጪ እየባከነ እንደሆነ ይገለጻል።

ከወጪ አንጻር ሲታይ ከክልል ወደ ፌዴራል ሲመጣ፣ በተለይም የክልሉ የስራ ቋንቋ ከፌዴራሉ የስራ ቋንቋ የተለየ በሆነበት ሁኔታ፣ ጉዳዩን ለፌዴራል ሰበር ለማቅረብ ሲባል ሰነዶችን ወደ ፌዴራል የስራ ቋንቋ ማስተርጎም የሚያስከትለው ወጪ ይኖራል። ከዚህም በተጨማሪ በሰበር ፊት የሚደረግ ክርክር መሰረታዊ የህግ ስህተት ለማሳየት የሚደረግ ጠለቅ ያለ የህግ ክርክር ስለሚሆን ባለጉዳዩ ራሱ የሚያከናውነው ሳይሆን የጠበቃ ድጋፍና ተሳትፎ የሚጠይቅ ስራ ነው። ጉዳዩ በክልል ደረጃ እያለ በጠበቃ ተይዞ የነበረ ቢሆንም እንኳ አንዳንዶ የክልሉ ጠበቃ የፌዴራል የጥብቅና ፈቃድ ስለማይኖረው፣ በክልል የጥብቅና ፈቃድም ቀርቦ መከራከር ስለማይፈቅድለት፣ ሌላ ጠበቃ ያውም "በማናቸውም ደረጃ የፌዴራል ፍርድ ቤት" ቀርቦ የመከራከር ፈቃድ ያለው መቅጠርን የግድ ይላል። ይህ ሁሉ ወጪ የባለጉዳዩን የመጓጓዣ፣ የስንቅና የማረፊያ ወጪዎችን ሳይጨምር ነው።ጥረቱ የሚሞገስ ቢሆንም ባለጉዳዩችን በዘመናዊ የመገናኛ መሳርያ ተጠቅሞ ባሉበት እንዲደመጡ ማድረግ ግን በቀላሉና በአጭር ጊዜ የሚሳካ ድርጊት አልሆነም።

ይህንን ችግር በመገንዘብ የስራ ባልደረባዬ የሆኑት አቶ ሙራዱ አብዶ በሌላ የህግ መጽሄትና[9] በሌላ ቋንቋ፣ ከጥቂት ዓመታት በፊት አንድ ሰፋ ያለ የምርምር ጽሁፍ

[9] Muradu Abdo: *Review of Decisions of state courts over State Matters by the Federal Supreme Court*, Mizan Law Review: Vol.I, No. 1(2007) pp. 60-74.

ያቀረቡ ሲሆን የችግሩን ስፋትና ለፌዴራል ስርዓቱ ያለው እንድምታ ከመጠቆም ባሻገር እስከ ህገመንግስት ማሻሻል ድረስ የሚዘልቅ የመፍትሄ ሃሳብ አቅርበዋል። አቶ ሙራዱ የህገ-መንግስቱን ድንጋጌዎች በጥሞና በማንበብና ህገ-መንግስቱ ሲረቀቅ የተዘጋጁ ቃለ ጉባኤዎች በጥልቀት በመመርመር የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር ሰበር ስልጣን በህገ-መንግስቱ የተሰጠው መሆኑን በማመን ህገ-መንግስቱን በማሻሻል የሰበር ሰበር ስልጣኑን መገደብ እንደሚገባ ሃሳብ አቅርበዋል።

አቶ ሙራዱ አብዶ የጠቀሱዋቸው ችግሮችና ስጋቶች የዚህ ጽሁፍ አቅራቢም ይጋራል። ነገር ግን ጽሁፍ አቅራቢው ህገ-መንግስቱ የሰበር ሰበር ሥልጣን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አልሰጠም፣ እንዲያውም ችግሩና ውዥንብሩ ህገ-መንግስቱን ከማሻሻል በመለስ መፍትሄ አለው ብሎ ያምናል። እንደሚታወቀው ህገ-መንግስት የማሻሻል ሂደት ረጅምና ውስብስብ ከመሆኑ የተነሳ በቀላሉና በአጭር ጊዜ የሚሳካ ድርጊት አይደለም። በተጨማሪም ህገ-መንግስቱን ማሻሻል ሳያስፈልግ ተፈላጊውን ግብ ማሳካት ከተቻለ፣ ለጋውን ህገ-መንግስት ገና በጨቅላ እድሜው ቀዶ ጥገና ውስጥ ማስገባት ተገቢም፣ ተመራጭም አይደለም።

ሆኖም እዚህ ላይ የሚነሳው ተገቢ ጥያቄ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የመጨረሻ በሆኑ ማናቸውም ጉዳዮች ላይ መሰረታዊ የህግ ስህተት ሲያጋጥም በሰበር የማየት ስልጣን በህገ-መንግስቱ የተሰጠው አይደለም ወይ? ህገ-መንግስቱን ከማሻሻል በመለሰሰ በምን ሊፈታ ይችላል? የሚል ይሆናል። ቀጥለን ስልጣኑ በህገ-መንግስቱ የተሰጠው እንዳልሆነ፣ ችግሩም የህገ-መንግስቱ እንዳልሆነና ህገ-መንግስቱን ከማሻሻል በመለስ ሊወገድ የሚችልበትን የመፍትሄ አቅጣጫ ለማሳየት እንሞክራለን።

ከዚህ በላይ የህገ-መንግስቱን አንቀጽ 80 አካል የሆኑ ሶስት ንኡሳን አንቀጾች ከህገ-መንግስቱ እንዳለ ወስደን አስቀምጠናል። እነዚህ ድንጋጌዎች በጥሞና ሲታዩ በህግ የሚዳኙ ጉዳዮችን 'የፌዴራል ጉዳዮች' 'የክልል ጉዳዮች'ና 'ማናቸውንም ጉዳዮች' በሚል ለያይተው ያስቀመጥዋቸው ሲሆን በ'ፌዴራል ጉዳዮች' የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ስልጣን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት፤ በ'ክልል ጉዳዮች' ደግሞ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ስልጣን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚሰጡ ናቸው።

ድንጋጌዎቹ ወደ ሰበር ጉዳይ ሲመጡ ግን የክልሉ ሰበር ሰሚ አካል መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበትን በክልል ጉዳይ የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ለማየት ስልጣን የሰጡት [10] ሲሆን የፌዴራሉ ሰበር ሰሚ አካል ግን መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበትን የፌዴራል ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ማናቸውንም የመጨረሻ ውሳኔ በሰበር ለማረም ስልጣን እንደተሰጠው ተመልክቷል።[11] የህገ-መንግስቱ ጉባኤ አባላት ከሰበር በፊት ላሉት ጉዳዮች የክልልና የፌዴራል ጉዳዮች እያሉ ሲከፋፈሉ ቆይተው የፌዴራሉን የሰበር ስልጣን ሲያመለክቱ ግን 'ማናቸውንም የመጨረሻ ውሳኔ' የሚል ሃረግ መጠቀማቸው የክልሉንም ሆነ የፌዴራሉ ጉዳይ የመጨረሻ ውሳኔ በፌዴራሉ ሰበር ሰሚ አካል እንዲታይ ስለፈለጉ ነው፣ የሚል መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ ነው። ይህም በሁለት

---

[10] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 80(3)(ለ)

[11] ዝኒ ከማሁ አንቀጽ 80(3)(ሀ)

ምክንያቶች ማጠናከር ይቻላል፡፡ አንደኛ የአንቀጽ 80(3) አቀራረጽ ይህንኑ የክርክር መስመር ያጠናክራል፡፡ ምክንያቱም ንኡስ አንቀጽ አንድና ሁለት የፌዴራሉን ለፌዴራል፣ የክልሉን ለክልል ከሰጡ በኋላ ንኡስ አንቀጽ ሶስት ከላይ የተጠቀሰው ቢኖርም በሚል የማፍረሻ ሐረግ መጠቀሙ የአጠቃላይ መርሁ ልዩ ሁኔታ መጥቀሉን የሚያመለክት ነው፡፡ ሁለተኛ ህገ-መንግስቱ ሲረቀቅ የተያዘው ቃለ ጉባኤም የፌዴራሉ ሰበር ሰሚ አካል የፌዴራል ጉዳዮችን ብቻ ሳይሆን ማናቸውንም (የክልል ጉዳዮችንም ጭምር) የመጨረሻ ውሳኔዎች በሰበር እንዲያይ ስልጣን የተሰጠው መሆኑ ያመላክታል፡፡[12]

ነገር ግን የህገ-መንግስቱ አንቀጽ 80(3)(ሀ) የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ስልጣን ይኖረዋል ብሎ አያበቃም፡፡ 'ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል' የሚል ተጨማሪ ሐረግም አለው፡፡ በህግ ያውም በህገ-መንግስት፣ የሚካተቱ ቃላት ሃረጎችና አረፍተ ነገሮች ታስበባቸው የተቀመጡ፣ ተገቢ ፋይዳና ዋጋ ሊሰጣቸው የሚገቡ ናቸው፡፡ ሃረግና አረፍተ ነገር ይቅርና ነጠላና ድርብ ሰረዝ መጠቀም የተለያየ ህጋዊ ውጤት ሊያስከትል ይችላል፡፡ ስለዚህ በዚህ ጸሃፊ እምነት 'ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል' የሚለው በንኡስ አንቀጹ ውስጥ ያለው ሃረግ ተገቢ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው፡፡ እሴት የማይጨምር ነገር ህገ-መንግስት ውስጥ ይካተታል ተብሎ አይታሰብምና፡፡በመሆኑም ዝርዝሩና ዋናው ቁም ነገር ማለትም በምን ጉዳዮችና(substantive) እንዴት(procedural) ሰበር ይቀርባል? የሚለው ለዝርዝር ህጎች የተተወ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ከዚህ አንጻር የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት የስልጣን ዳር ድንበር በተሟላ ሁኔታ ለመለየትና ለመከለል ይቻል ዘንድ አግባብነት ያላቸው 'ዝርዝር ህጎች' ማፈላለግ ይገባል ማለት ነው፡፡ በተለይም የክልል ዳኝነታዊ ጉዳይ በመርህ ደረጃ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስልጣን በመሆኑ፣ ፌዴራሉ የዳኝነት አካል በክልል ጉዳዮች እንዲገባ መፈቀዱ የመርሁ ልዩ ሁኔታ ስለሆነ በጠባቡ መፈጸምና መተርጎም ያለበት ነው፡፡ የህግ አተረጓጎም መርህም የሚያስገነዝበን ይህንኑ ነው(Exceptions should be interpreted narrowly)፡፡ ይህም ማለት በዝርዝር ህግ ውስጥ በግልጽ ባልተሰጠ ነገር ፌዴራሉ የሰበር ስልጣን አይኖረውም ማለት ነው፡፡

ስለዚህ ቀጣይ ስራችን የሚሆነው በዚህ ረገድ ዝርዝር ህጎች አሉን ወይ? የሚል ነው፡፡ መልሱም አዎንታ ነው፡፡ እንደሚታወቀው ህገ-መንግስቱ ከጸደቀ ከአንድ አመት በኋላ 'በአዋጅ ቁጥር 25/1988' የሚታወቅ 'የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ' የታወጀ ሲሆን በዚሁ አዋጅ ውስጥ የፌዴራሉ ፍርድ ቤቶች እርከንና የስልጣን ወሰን የሚያመለክቱ ድንጋጌዎች ተካትተውበታል፡፡ ከእነዚህም አንዱ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ስልጣን የሚያመለክት በአዋጁ በአንቀጽ 10[13] ሥር ተደንግጎ ይገኛል፡፡ እንደሚከተለውም ይነበባል፡፡

---

[12] Muradu Abdo, *Supra note* at 9, p.69.

[13] አዋጁ በአንቀጽ 22 ሥር ሰበር እንዴት ይቀርባል? ለሚለው ጥያቄ መልስ ይሰጣል፡፡

*የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለባቸውን የሚከተሉትን ጉዳዮች በሰበር የማየት ስልጣን ይኖረዋል።*

*1. በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠባቸውን ጉዳዮች፤*

*2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠባቸውን ጉዳዮች፤*

*3. የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት <u>መደበኛ ችሎት</u> ወይም <u>በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሳኔ</u> የሰጠባቸውን ጉዳዮች ናቸው።(ሠረዝ የተጨመረ)*

ከእነዚህ ንኡሳን አንቀጾች መገንዘብ የሚቻለው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸው ጉዳዮች ወደ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከሶስት አቅጣጫ ሊቀርቡ ይችላሉ። አንደኛው መንገድ ከፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በቀጥታ ወደ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሚቀርቡ ጉዳዮች ይኖራሉ። ለምሳሌ በአሰሪና ሰራተኛ ህግ መሰረት የግልም ሆነ የወል የስራ ክርክር የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጥባቸው በከፍተኛ ፍርድ ቤት ደረጃ ነው።[14] ስለሆነም እንዲህ አይነቶቹ ውሳኔዎች መሰረታዊ የህግ ስህተት እንዳለባቸው ከታመነ ወደ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት መቅረብ ሳይኖርባቸው በቀጥታ ወደ ፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ያመራሉ ማለት ነው። ሁለተኛው መንገድ ከፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ከራሱ በመደበኛ ችሎቱ በሶስት ዳኞች ተሰይሞ የሚያስተናግዳቸው በአዋጁ በአንቀጽ 8 በመጀመሪያ ደረጃ (original jurisdiction) የዳኝነት ስልጣኑ ወይም በአንቀጽ 9 መሰረት በይግባኝ (appellate jurisdiction) ሰሚነቱ አይቶ ውሳኔ ያሳረፈባቸው ጉዳዮች እንዲሁ መሰረታዊ የህግ ስህተት ከተገኘባቸው በፌዴራል ሰበር ሰሚው ችሎት የሚመረመሩ ይሆናሉ። ሦስተኛውና የመጨረሻው በዚህ አዋጅ የተመለከተው መንገድ፣ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣናቸው ወይም በይግባኝ አይተው የመጨረሻ ውሳኔ የሰጡባቸው ጉዳዮች እንዲሁ መሰረታዊ የህግ ስህተት ከተፈጸመባቸው በፌዴራሉ ሰበር ችሎት የሚታዩ ናቸው።

ህገ-መንግስቱም ሆነ አዋጁ 'የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠባቸው ጉዳዮች' ሲሉ በሰበር የታዩትን እንደማይጨምር ከቃላት አጠቃቀማቸው መገንዘብ ይቻላል። ሁለቱም ሰነዶች የሚጠቀሙት አገላለጽ 'የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠባቸው ጉዳዮች መሰረታዊ የህግ ስህተት ከተገኘባቸው በሰበር ይታያሉ' በሚል ሲሆን ይህም ሰበርንና የመጨረሻ ውሳኔን ለያይቶ ያስቀመጠ አገላለጽ ነው በመሆኑም ሰነዶቹ 'የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠባቸው ጉዳዮች' ሲሉ ከሰበር በመለስ ህጉ በሚፈቅደው ስርዓት መሰረት የይግባኝ 'ጣጣቸውን'

[14] የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/1996 መሰረት የግል የስራ ክርክር ከክልል የመጀመሪያ ደረጃ (ወረዳ) ፍርድ ቤት ተነስቶ በክልል ይግባኝ ሰሚ (ዞን ወይም ከፍተኛ) ፍርድ ቤት ያበቃል (አንቀጽ 139(2))። የወል የስራ ክርክርም ከአሰሪና ሰራተኛ ወሳኝ ቦርድ ተነስቶ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ላይ ያበቃል (አንቀጽ 154(2)) በሁለቱም መንገድ ዞሮ ዞሮ ማብቂያው የክልል ወይም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው። በርግጥ ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ከቦርዱ የተለየ ውሳኔ ቢሰጥ ወደ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ እንዲቀርብ አይፈቀድም ወይ? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። ይህ ነጥብ በሌላ ጊዜ በሌላ ርእስ የሚታይ ይሆናል።

የጨረሱ ለማለት ሲሆን አንዳንዴ ይግባኝ የማይባልባቸው ጉዳዮችም ሊኖሩ ይችላሉ። ለነገሩ 'የመጨረሻ ውሳኔ' የሚለው ሃረግ ሰበርን እንዲጨምር ተፈልጎ ቢሆን ኖሮ የመጨረሻ ውሳኔ ከተባለ በኃላ ተመልሶ ሰበር የሚል ቃል መጠቀም ባላስፈለገ ነበር።

ከዚህም በተጨማሪ በእለት ተእለት የህግ ቃላት አጠቃቀም አንጻርም ሲታይ 'የመጨረሻ ውሳኔ' ሲባል የመጨረሻው ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ ማለት ነው። ሰበር መደበኛ የክርክር ሂደት ባለመሆኑና በልዩ ሁኔታ ብቻ የሚፈቀድ የክርክር ስርዓት በመሆኑ በዚህ ስሌት ውስጥ የሚገባ አይደለም። የመጨረሻ ውሳኔ ሲባል ሰበርንም ይጨምራል ከተባለ ግን ሁሉም ጉዳዮች በሰበር በኩል አልፈው ይጠናቀቃሉ፤ ሰበር ላይ ደርሰው 'ቁርጡ እስካልታወቀ' ግን የመጨረሻ ውሳኔ ተደርገው አይወሰዱም፣ ወደሚል መደምደሚያ እንዳይወስደን ያሰጋል። ስለዚህ የመጨረሻ ውሳኔ ሲባል ከሰበር በመለስ ባለ ስርዓት የታዩትን እንጂ በየትኛውም መድረክ በሰበር የታዩትን እንደሚጨምርም ተደርጎ ሊተረጎም አይገባም ባዮች ነን።

ምናልባት 'የመጨረሻ ውሳኔ' ሲባል ሰበርንም ይጨምራል ከተባለም ሌላ የመከራከሪያ ነጥብ ማቅረብ ይቻላል። በአዋጅ ቁጥር 25/1988 መሰረት ከክልል ተነስተው በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ስልጣን ስር ይወድቃሉ ተብለው የተመለከቱት ጉዳዩች ሁለት ሲሆኑ እነዚህም 'የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት <u>በመደበኛ ዳኝነት</u> ወይም <u>በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠባቸው ጉዳዮች'</u> ብቻ ናቸው።[15] (*ሠረዝ የተጨመረ*)

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ህገ-መንግስቱ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶችም ቢሆኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት ለማረም በክልላቸው የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ማደራጀት እንደሚችሉ አመልክቷል። ስለሆነም የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ጉዳዮችን ሲመረመሩ እንደነገሩ ሁኔታ በሦስት ደረጃ ማለትም በመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ስልጣን (original jurisdiction) ወይም በይግባኝ ደረጃ (appellate jurisdiction) እንዲሁም በሰበር ደረጃ (cassation proceeding) ሊሆን ይችላል ማለት ነው። ከዚህ አንጻር በፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ይመረመሩ ዘንድ መስተናገድ የሚገባቸው በመጀመሪያ ደረጃ ዳኝነት ወይም በይግባኝ ደረጃ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የታዩትን እንጂ በክልል ደረጃ በሰበር የታዩትን ጉዳዮች በተመለከተ በአዋጁ ውስጥ የተባለ ነገር የለም።

አዋጁ ዝምታ በመረጠበት ሁኔታ መወሰድ ያለበት የህግ ግምት ምን ሊሆን ይገባል? ብሎ መጠየቅና መልስ መሻት ተገቢነት ያለው ነጥብ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ ቀደም ሲል እንደገለጽነው ሰበር ጠባብ ስርአት ነው። ማንኛውም የህግ ስህተት በሰበር ስርአት እንዲያልፍ የሚፈቅድ የህግ አካሄድ የለንም። በሰበር የመደመጥ እድል ከይግባኝም በእጅጉ የጠበበ ሲሆን ማናቸውም ባለጉዳይ የይግባኝ ያህል እንደ መብት የሚጠይቀው አይደለም። በሰበር ሰሚ ፍርድ ቤት እጅ ያለ ስልጣን (judicial discretion) ነው ምክንያቱም መሰረታዊ የህግ ስህተት አለ የለም ብሎ የመወሰን ብቸኛና የመጨረሻ ውሳኔ እርሱ ነውና። ስለሆነም ህጉ ዝምታ ከመረጠ ሰበርን ፈቅዷል ተብሎ ሊወሰድ አይችልም። ሁለተኛ እላይ እንደተመለከተው የፌዴራሉ የዳኝነት አካል የክልሉ የዳኝነት ዘርፍ የበላይ አካል ባለመሆኑ በግልጽ የተመለከተ የህግ ስልጣን ባልተሰጠበት ሁኔታ

---

[15] 'የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ' ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10(3)

ክልሉ በስልጣኑ ያከናወነውን ዳኝነት የሚመረመርበት የህግ መሰረት አይኖረውም። በሶስተኛ ደረጃ በህገ-መንግስቱ ውስጥ "ለፌዴራሉ መንግስት በተለይ ወይም ለፌዴራሉ መንግስትና ለክልሎች በጋራ በግልጽ ያልተሰጠ ስልጣን የክልል ስልጣን ይሆናል' የሚል ህገ-መንግስታዊ መርህ አለን። ከዚህ መርህም አንጻር ህገ-መንግስቱ 'በዝርዝር ህግ ይወሰናል' ካለ በኋላ፣ ዝርዝር ህጉ ዝምታ ከመረጠ የፌዴራል ሰበር ሰሚው አካል የሰበር ሰበር የሚያከናውንበት የህግ ድጋፍ የለውም ማለት ነው። ሲጠቃለልም እላይ ለመንደርደሪያነት የተጠቀምንበት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር ችሎቱ መርምሮ እልባት የሰጠበትን ጉዳይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አስቀርቦ እንደገና በሰበር መመርመሩ የህግ ድጋፍ የሌለውና የፌዴራልና የክልል የስልጣን ክፍፍሉን ያላገናዘበ አሰራር ነው ብለን እናምናለን።

በርግጥ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት ባላደራጀበት ሁኔታ የመጨረሻ ውሳኔው መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት ከተባለ በፌዴራል ሰበር ሰሚው መመርመርን እላይ በተጠቀሰው አዋጅ መሰረት አይከለከልም። ለምሳሌ የሶማሌ ክልልና የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤቶች እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የክልል ሰበር ሰሚ ችሎት እንዳላደራጁ ይታወቃል። ስለሆነም የእነዚህ ክልሎች ጉዳዮች በህገ-መንግስቱና በዝርዝር ህጉ መሰረት በፌዴራሉ ሰበር ሰሚ ሊመረምሩ የሚችሉ መሆናቸውን መገንዘብ ይገባል።

በኛ እምነት ይህ አይነቱ አተረጓጎምና አረዳድ አንዳንድ ባለጉዳዮች የሰበር ሰበር 'ተጠቃሚ' ሌሎች ግን በአንድ ሰበር ብቻ እጣ ፈንታቸው የሚወሰንበት ወጥነት የሌለው አሰራርንም ያስወግዳል። ይህም 'ሰዎች ሁሉ በህግ ፊት እኩል ናቸው' ከሚለው ህገ-መንግስታዊ መርህም ጋር የተጣጣመ አተረጓጎም ነው። ስለዚህ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥልጣን ያልተገደበ አይደለም ብቻ ሳይሆን እንዲያውም ሥልጣኑ በዝርዝር ህጎች በግልጽ በተቀመጡ ጉዳዮች ላይ ብቻ የተገደበ ነው የሚል እምነት አለን።

ቀጣዩ ስራችን ከአዲስ አበባ ከተማ የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት ተነስቶ በከተማው አስተዳደር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በይግባኝ ደረጃ ተመርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠበትን ጉዳይ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት አስቀርቦ መመርመሩስ ምን የህግ መሰረት አለው? የሚለውን ማየት ነው። ቀደም ብለን እንዳየነው በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ስር በተመለከተው አንቀጽ ስር ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች 'ጣጣቸውን የጨረሱ' ጉዳዮች በፌዴራሉ ሰበር ሰሚ አካል ሊመረመሩ የሚችሉበት እድል የሚጠቁም ድንጋጌ የለውም። ሰበር ሰሚው ችሎት ከፌዴራል ወይም ከክልል ፍርድ ቤቶች የሚነሱትን የመጨረሻ ውሳኔ ያገኙ ጉዳዮች ብቻ እንደሚያስተናግድ አይተናል።

በርግጥ 'ክልል' ሲባል በህገ-መንግስቱ በክልልነት የሚታወቁትንና አዲስ አበባ መስተዳድርንና ድሬዳዋ ካውንስልን ይጨምራል ሲባል ይችል ይሆናል። አንዳንድ አዋጆችም 'ትርጓሜ' በሚለው የአዋጁ ክፍል ይህንኑ በማካተት ችግሩን ለመፍታት ጥረት ሲያደርጉ ይስተዋላል። ነገር ግን አዋጅ ቁ. 25/1988 'ክልል' የሚለው ቃል ለአዋጁ አፈጻጸም ሲባል እላይ በተመለከተው መልክ እንዲተረጎም መመሪያ አልሰጠም። በመሆኑም 'የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠባቸው ጉዳዮች' የሚለው ሃረግ፣ አዲስ አበባም ክልል ማለት ነውና 'የአዲስ አበባ መስተዳድር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ

ቤት የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠባቸው ጉዳዮች' ተብሎ ሊተረጎም ይችላል ብሎ መከራከር ሚዛን የሚደፋ ክርክር አይሆንም፡፡ ስለዚህ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ከአዲስ አበባ መስተዳድር ማህበራዊ ፍርድ ቤት የተነሳውን ክርክር በሰበር አቅርቦ የመረመረው ከአዋጅ ቁጥር 25/1988 ከመነጨ ስልጣን አይደለም ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ሌላ የስልጣን ምንጭ ካልተገኘለት በቀር ከስልጣኑ ውጪ ያከናወነው ድርጊት ነው ተብሎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

ሆኖም 'ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል' የሚለው ሃረግ አንድ አዋጅን ብቻ አይተን እንድንደመድም የሚያስገድደን አይሆንም፡፡ ለዚህ ስልጣን አግባብነት ያላቸው የህግ መሰረቶች በተለያዩ ህጎችና በተለያዩ ጊዜያት እየወጡ ተጨማሪ የሰበር ስልጣን መሰረቶች ከመሆን የሚያግድ አይደለም፡፡ ስለዚህ በሌሎች ህጎችም ቢሆን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተጨማሪ የሰበር ስልጣን የሚሰጡ ህጎች ካሉ አፈላልጎ ማግኘት ግንዛቤአችንን የሚያሰፋው ከመሆን አልፎ የሰበር ሰሚው የስልጣን ወሰንን በተሟላ ሁኔታና በአግባቡ ለመገንዘብ ይረዳናል፡፡

ከዚህ አንጻር 'የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር' አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 42(3) አሁን ለያዝነው ጉዳይ አግባብነት ያለው ነው፡፡ እንደሚከተለውም ይነበባል፡፡ *'በአዲስ አበባ ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለው የሚል ወገን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር አቤቱታ ማቅረብ ይችላል'* ይላል፡፡ 'መጨረሻ ውሳኔ' የሚባለውም በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ እንደሆነ በዚያው አዋጅ ውስጥ ተመልክቷል፡፡[16] በመሆኑም ምንም እንኳ አዋጅ ቁጥር 25/1988 የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ፍ/ቤቶች የሰጡትን የመጨረሻ ውሳኔ በሰበር ለመመርመር የማያስችለው ቢሆንም በአዋጅ 361/1995 መሰረት ተጨማሪ ስልጣን የተሰጠው በመሆኑ ቀደም ሲል ለውይይት መነሻነት የተጠቀምንበት የሰበር መዝገብ ቁ. 31601 አስቀርቦ መመርመሩ ህጋዊነት ያለው ድርጊት መሆኑን መገንዘብ ይገባል፡፡

ከዚህ በላይ የጠቀስናቸው ሁለት አዋጆች የህገ-መንግስቱ አርቃቂዎች በፌዴራል ደረጃ በሰበር የሚታዩት ጉዳዮች 'በዝርዝር ህግ ይወሰናሉ' ብለው ለገቡት ቃል በከፊል መልስ የሰጡ ሲሆን ሌሎች ዝርዝር ህጎችም ቢሆኑ እንዲሁ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለው ድንጋጌ ይዘው ሊወጡ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ በአዋጅ ቁጥር 27/1988 የሚታወቀው 'የመከላከያ ሰራዊት አዋጅ' በአንቀጽ 32 ስር *'በቀዳሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚ ወታደራዊ ፍርድ ቤት የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ ሲገኝ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በሰበር የማየት ስልጣን አለው'* የሚል ድንጋጌ ይገኝበታል፡፡ ይህም ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ተጨማሪ የስልጣን ምንጭ ነው፡፡ እንዲህ እንዲህ እያለ በዝርዝር ህጎች ውስጥ የስልጣን መሰረት የሆኑ ድንጋጌዎች ማፈላለግ የሚቻል ሲሆን በዝርዝር ህግ የሰበር ስልጣን ባልተሰጠበት ሁኔታ ግን የመጨረሻ ውሳኔ በተሰጠባቸው ጉዳዮች ላይ ሁሉ ያልተገደበ የሰበር ስልጣን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተሰጥቷል የሚለው አተረጓጎምና አፈጻጸም የህገ-መንግስቱን ቃላትና መንፈስ የተከተለ አይደለም እላለን፡፡ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ያልተገደበ ስልጣን ቢኖረው ኖሮ በሦስቱ አዋጆች የተመለከቱት 'የፌዴራል ጠቅላይ

[16] የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ አንቀጽ 43(5)

ፍርድ ቤት በሰበር የማየት ስልጣን ይኖረዋል' የሚሉ ድንጋጌዎችና 'ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል' የሚለው ሃረግ በህገ-መንግስቱ ውስጥ ማስቀመጥ አስፈላጊ ባልሆነ ነበር፡፡

## 6. ማጠቃለያ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በዝርዝር ህግ በሰበር እንዲያይ ስልጣን ሳያገኝ እየመረመራቸው ያሉት የክልል ጉዳዮች ከስልጣኑ ውጪ በመሆኑ መቆምና ማብቃት ያለበት ድርጊት ነው፡፡ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት የሰበር ሰበር እንዲያከናውን ያስገደደው የህገ-መንግስቱ ድንጋጌዎች አጻጻፍ የፈጠረው ችግር ነው ሲባል አልፎ አልፎ ይደመጣል፡፡ መፍትሄውም በህገ-መንግስቱ ድንጋጌዎች ላይ የማሻሻያ ስራ ማከናወን ነው እየተባለ ይነገራል፡፡ በዚህ ፀሐፊ እምነት ግን ችግሩ የህገ-መንግስቱ አጻጻፍ ሳይሆን የህገ-መንግስቱ አነባበብ ችግር ነው፡፡ መፍትሄውም ህገ-መንግስቱን ማሻሻል ሳይሆን ህገ-መንግስቱን ባግባቡ ማንበብ፤ ከዝርዝር ህጎችም ጋር አገናዝቦ መመርመር ነው፡፡ በዚህ ፀሐፊ እምነት ችግሩ የተፈጠረው 'ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል' የሚለው ሃረግ ሳይነበብ እየቀረና የሰበር ስልጣኑ ያለገደብ የተሰጠ እንደሆነ ተደርጎ በመወሰዱ ነው፡፡ የህገ-መንግስቱ ጉባኤ አባላት የፌዴራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ያልተገደበ የመጨረሻ ውሳኔዎች በሰበር የመመርመር ስልጣን ሊሰጡት አስበው ቢሆን ኖሮ 'ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል' በማለት በቀጠሮ ማሳደር አስፈላጊ አልነበረም፡፡

'ታሪክ ራሱን ይደግማል' እንዲሉ በንጉሱ ዘመን በፍርድ ቤት ክርክር ሂደት የተቋጨን ጉዳይ እድሉ ከተገኘና 'አዲስ አበባ ሄዶ 'ዙፋን ችሎት' ፊት መቅረብ ከተቻለ ፍትህ ይገኛል' እየተባለ ብዙ ህዝብ ፍትህ የማይገኝን ፍለጋ ተንከራትቷል፡፡ በደርግ ዘመንም ግፍ የሚፈጽሙት የበታች ሹማምንት ናቸው፡፡ እንደምንም ተብሎ 'ሰውየው' (ኮሎኔል መንግስቱን ማለት ነው) ጋር ከተደረሰ ፍትህ ይገኛል እየተባለ፤ አልፎ አልፎም ራሳቸው 'ሰውየው' የሚያነሱት የስልክ ቁጥር፣ ራሳቸው 'ሰውየው' የሚቀበሉት ቴሌግራም አለ እየተባለ፤ የብዙ የፖለቲካ እስረኞች ቤተሰቦች 'የሰውየው' ን የስልክ ቁጥርና ቴሌግራም ፍለጋ አሳር መከራቸውን አይተዋል፡፡[17] የ'ዙፋን ችሎት'ና የ'ሰውየው' ቋሚ አድራሻም አዲስ አበባ እንደነበረ ይታወቃል፡፡

ይህንን አዲስ አበባን የፍትህ የመጨረሻ ምንጭ አድርጎ የመውሰድ ስነ-አእምሮ በማህበረሰባችን ህሊና ውስጥ ተቀርጾና ዘልቆ ገብቶ ባለበት ሁኔታ አዲስ አበባ 'መናገሻ ከተማውን' ያደረገው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፤ በክልል ደረጃ በሰበርም ጭምር ታይቶ ያበቃለትን ጉዳይ አስቀርቦ ይመራምራል ሲባል፤ ፍትህ አላገኘሁም ብሎ ያመነ ሁሉ የእርሻ በሬውን ሳይቀር ሸጦ እንደተለመደው ወደ አዲስ

---

[17] በወቅቱ በአንድ የክፍለ ሃገር ከተማ ውስጥ በጸረ አብዮተኝነት የተጠረጠረ ወጣት በአደባባይ በተደረገ 'የአብዮቱ ወገኖች' ስብሰባ በሞት እንዲቀጣ ተወስኖበት የፍርዱን አፈጻጸም ሲጠባበቅ በነበረበት ወቅት፤ የወጣቱ ወላጅ አባት ወደ 'ሰውየው' ቴሌግራም ልከውና ተሳክቶላቸው ልጃቸውን ከሞት ሊያተርፉ ችለዋል፤ እየተባለ ሲወራ እንደነበር የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ በአንክሮ ያስታውሳል፡፡ ከሞት የተረፈው ወጣት በህግ ትምህርት ተመርቆ አሁንም በህይወት ይገኛል፡፡

አበባ መከተቱ አይቀርም። ፌዴራል መዋቅሩ ግን እንዲህ ዓይነት ስሜትና ውጤት እንዲከተል ሳይሆን እንዲወገድ ታስቦ የተደራጀ እንደሆነ ይታመናል። የህገ-መንግስቱ ጉባኤ አባላትም ቢሆኑ ይህንኑ ውጤት ለማግኘት አስበውና ፈቅደው ህገ-መንግስቱን ቀርጸዋል ለማለት ያስቸግራል።

ስለዚህ ከዚህ በላይ የቀረበው የህግ አተረጓጎም ዘይቤና የመፍትሄ ሃሳብ ተቀባይነት ሊሰጠው ይገባል ምክንያቱም አተረጓጎሙ፦

- ከህገ-መንግስቱ ቃላትና መንፈስ ጋር የተጣጣመ፤
- የፌዴራልና የክልል መንግስታት ስልጣን ክፍፍልን ያገናዘበ፤
- ሰዎች ሁሉ በህግ ፊት እኩል መሆናቸውና እኩል እድል ያላቸው መሆኑን ያረጋገጠ፤
- የዜጎችን ጊዜና ወጪ ብሎም መንገላታትን የሚቀንስ፤
- የመጨረሻው የፍትህ ምንጭ 'ማዕከላዊው መንግስት' ነው የሚለው የአሃዳዊ መንግስት ስነ-አእምሮ የፈጠረው ጠባሳም የሚፍቅ፤
- ለፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎትም ቢሆን የጉዳይና የባለጉዳይ ጫና በእጅጉ በመቀነስ ውጤታማና ጥራት ያላቸው ስራዎች እንዲያከናውን በር የሚከፍትለት ይሆናል ተብሎ ይታመናል።

የጉዳይ ጫና ሲቀነስለት ሰበር ችሎቱ ከተለያየ አቅጣጫ ተመዝነውና በቂ ጊዜ ተመድቦላቸው የሚሰጡ ውሳኔዎች ለማዘጋጀት አመቺ ሁኔታ ስለሚፈጠርለት በአዋጅ ቁጥር 454/1997 የተጎጸናፈው 'የመጨረሻና አስገዳጅ የህግ ትርጉም' የመስጠት ስልጣኑን የተፈረደለት ብቻ ሳይሆን የተፈረደበት ባለጉዳይም ጭምር 'የሚረካበት' ውሳኔ በማስተላለፍ እንዲወጣው ያስችለዋል። የፍትህ የመጨረሻና የመዳረሻ ግብም ይህ ነው።